# <u>አዋጅ ቁጥር ....../2014</u>

# <u>የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነት እና አለመግባባት የሚታይ በመሆኑ፤ ይህንን ልዩነት እና አለመግባባት ለማርገብ እና ለመፍታት ሰፋፊ አገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ በማካሄድ አገራዊ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

መሠረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አካታች አገራዊ ምክክሮችን ማካሄድ የተሻለ አገራዊ መግባባትን ለመገንባት እና በሂደትም የመተማመንን እና በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተቀራርቦ የመሥራት ባህልን ለማጎልበት፣ እንዲሁም የተሸረሸሩ ለማሳለጥ የሚያስችል ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

አገራዊ ምክክሮች ተቀባይነት እና ተዓማኒነት ያላቸው እንዲሆኑ ከሚያስችላቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ምክክሮቹን የሚያመቻቸውና የሚመራው አካል ብቃትና ገለልተኝነት በመሆኑ፤ ምክክሮቹን በብቃትና በገለልተኝነት ለመምራትና ለማስተባበር የሚችል ሰፊ ቅቡልነት ያለው ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታዉጇል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

https://chilot.me

ይህ አዋጅ **“የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር....../2014”** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ **“የኮሚሽኑ ምክር ቤት”** ማለት ሁሉንም የአገራዊ ምክክር አመቻች ኮሚሽነሮችን በአባልነት ያቀፈ የኮሚሽኑ ምክር ቤት ነው፤

2/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን፤ የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

3/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

**3. የአገራዊ ምክክሩ መርሆዎች**

1/ አገራዊ ምክክሩ እና አጠቃላይ የኮሚሽኑ ስራዎች የሚመራባቸው መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

(ሀ) አካታችነት፤

(ለ) ግልፅነት፤

(ሐ) ተዐማኒነት፤

(መ) መቻቻል እና መከባበር፤

(ሠ) ምክንያታዊነት፤

(ረ) የምክረ ሃሳቦች ተግባራዊነት እና አውድ ተኮርነት፤

(ሰ) ገለልተኛ አመቻች፤

(ሸ) የአጀንዳዎች ጥልቀት እና አግባብነት፤

(ቀ) ዲሞክራሲ እና የሕግ የበላይነት።

2/ የኮሚሽኑ ምክር ቤት አስፈላጊ ናቸው በማለት የሚያምንባቸውን መርሆዎች በተጨማሪነት ሊያካትት ይችላል።

## ክፍል ሁለት

## ስለኮሚሽኑ መቋቋም፣ ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ተግባር እና ኃላፊነቶች

https://chilot.me

**4. መቋቋም**

1/ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) ከፖለቲካ ወገንተኝነት፣ ከማንኛውም የመንግሥት ወይም ሌላ አካል ተጽዕኖ ነፃ የሆነ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል።

**5. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ክልሎች ቅርንጫፍ ፅሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

**6. የኮሚሽኑ ዓላማ**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት መሠረታዊ ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1/ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል መሠረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ለተፈጠሩ ልዩነቶች ወሳኝ ምክንያቶችን በመለየት እና ውይይቶቹ የሚካሄዱባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በመለየት ምክክር እንዲደረግባቸው ማመቻቸት፤

2/ የሚካሄዱት አገራዊ ምክክሮች አካታች፣ ብቃት ባለውና ገለልተኛ በሆነ አካል የሚመሩ፣ የአለመግባባት መንስዔዎችን በትክክል በሚዳስስ አጀንዳ የሚያተኩሩ፣ ግልፅ በሆነ የአሠራር ሥርዓት የሚመሩ እና የምክክሮቹን ውጤቶችን ለማስፈፀም የሚያስችል ዕቅድ ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ውጤታማ የሆኑ አገራዊ የምክክር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ፤

3/ የሚካሄዱት አገራዊ ምክክሮች በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እንዲሁም በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበትና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ውይይቶቹ እንዲካሄዱ ሥርዓት መዘርጋት፤

4/ ከምክክሮቹ የተገኙ የመፍትሔ ምክረ ሃሳቦች በሥራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ በማድረግ በዜጎች መካከል እንዲሁም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መተማመን የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲገነባ ማስቻል፤

5/ ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡ ውስጣዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ባህል ለማዳበር እና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ምቹ መደላደል መፍጠር፤

https://chilot.me

6/ ወቅታዊ ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ተፈተው አስተማማኝ ሰላም የሚረጋገጥበትን የፖለቲካ እና የማኅበራዊ መደላደል ማመቻቸት፤

7/ ለአገራዊ መግባባት እና ጠንካራ ቅቡልነት ያለው አገረ መንግሥት ለመገንባት ፅኑ መሠረት መጣል ናቸው።

## 7. <u>የኮሚሽኑ አደረጃጀት</u>

ኮሚሽኑ፡-

1/ የኮሚሽኑ ምክር ቤት ፤

2/ ዋና ኮሚሽነር ፤

3/ ምክትል ዋና ኮሚሽነር፤

4/ ፅሕፈት ቤት፤

5/ አስፈላጊ ኮሚቴዎች፤ እና

6/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

## 8. <u>የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን</u>

1/ የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን ሦስት (3) ዓመት ነው።

2/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊራዘም ይችላል።

3/ የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን የሚቆጠረው በዚህ አዋጅ መሠረት የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

## 9. <u>የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ ምክክሮችን የሚያመቻቹና የሚያስፈፅሙ፣ የተለያዩ ጥናቶችን የሚያካሄዱ እና የምክረ ሃሳቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎችን እና የባለሞያ ቡድኖችን ያቋቁማል፤

2/ ከዚህ በፊት በመንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተደረጉ አገራዊ የምክክር ሂደቶችን እና የተገኙ ውጤቶችን ያጠናል፣ በቀጣይ በሚያካሄዳቸው አገራዊ ውይይቶች በግብዓትነት ይጠቀማል፤

https://chilot.me

3/ በልሂቃኖች መካከል አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያሉትን ልዩነቶች በጥናት፣ በሕዝባዊ ውይይቶች ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መንገዶች በመጠቀም ይለያል፤

4/ የምክክር አጀንዳዎችን ይቀርፃል፣ ምክክር እንዲደረግባቸው ያመቻቻል፣ ምክክሮችን እና ውይይቶችን ያሳልጣል፤

5/ ከመላ ሀገሪቱ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እና አካላትን የሚወክሉ ተሳታፊዎች የሚሳተፉባቸው፣ አገራዊ መግባባት ለማምጣት የሚያስችሉ የተለያዩ የምክክር ስብሰባዎችን በፌዴራል እና በክልሎች ደረጃ እንዲካሄዱ ያመቻቻል፤

6/ በአገራዊ የምክክር ጉባዔ ላይ የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን ግልፅ በሆኑ መሥፈርቶች እና የአሠራር ሥርዓት መሠረት ይለያል፣ በምክክሮች ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

7/ ምክክሮቹ በኮሚሽነሮች ወይም የኮሚሽነሮች ምክር ቤት በሚሰይማቸው አወያይዮች አማካኝነት እንዲመሩ ያደርጋል፤

8/ በምክክር ሂደቶች የሚደረጉ ምክክሮችን ቃለ ጉባዔ የሚይዙ፣ የቀረቡ ምክረ ሃሳቦችን የሚያጠናቅሩ እና አደራጅተው ለኮሚሽነሮች ምክር ቤት የሚያቀርቡ ባለሙያዎችን ይመድባል፣

9/ የፅሕፈት ቤቱን የውስጥ የአሠራር ሥርዓት፣ የምክክር አጀንዳዎች ወይም አርዕስት የሚመረጡበትን የሚመለከት፣ በአገራዊ ውይይቶች ላይ የሚሳተፉ አካላት የሚለዩበትን ሥርዓት ለመዘርጋትና መሰል ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ ውስጠ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

10/ የአገራዊ ምክክር ጉባዔ አጀንዳዎችን፣ የምክክሮቹን ሂደት፣ በምክክሮቹ የተገኙ ምክረ ሃሳቦችን እንዲሁም ምክረ ሃሳቦቹ በተግባር ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሥልት የሚገልፅ ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት ለመንግሥት ያቀርባል፣ ለህዝብም ይፋ ያደርጋል፤

11/ መንግሥት ከአገራዊ ውይይቶች የሚገኙ ምክረ ሃሳቦችን በተግባር ላይ ለማዋል እንዲችል ግልፅ እና ተጨባጭ የሆነ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

12/ የምክረ ሃሳቦቹን ተግባራዊነት ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

13/ አላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

https://chilot.me

10. <u>የኮሚሽኑ ምክር ቤት ስብሰባ</u>

1/ የኮሚሽኑ ምክር ቤት በውስጥ አሠራር ደንቡ መሠረት መደበኛ ስብሰባ ያካሄዳል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ጥሪ ወይም ከኮሚሽነሮቹ መካከል (50+1) የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ጥያቄ ሲያቀርቡ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤

2/ ከኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች መካከል (50+1) ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

3/ የኮሚሽኑ ውሳኔዎች በኮሚሽኑ ምክር ቤት ላይ ከተገኙ ኮሚሽነሮች በአብላጫ ድምፅ ያልፋሉ፤

4/ በኮሚሽኑ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ድምፅ እኩል ለእኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምፅ ወሳኝነት ይኖረዋል፤

5/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የኮሚሽኑ ምክር ቤት የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለ ኮሚሽነሮች</u>

11. <u>ስለኮሚሽነሮች</u>

1/ ኮሚሽኑ አሥራ አንድ (11) ኮሚሽነሮች ይኖሩታል፤

2/ የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር፤ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ሌሎች ኮሚሽነሮች በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፤

3/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሹመት ውሳኔውን የሚሰጠው የቀረቡት ዕጩዎች በዚህ አዋጅ አንቀፅ 13 ሥር የተቀመጡ መሥፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ይሆናል።

12. <u>የኮሚሽነሮች አሰያየም</u>

የኮሚሽነሮች አሰያየም በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

1/ ጠቅላይ ሚኒስትር ፅሕፈት ቤት ዕጩ የኮሚሽን አባላትን ከሕዝብ፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሲቪል ማኅበራት ኮሚሽነር ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦችን ጥቆማ ይቀበላል፤

https://chilot.me

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ሥር በተቀመጡት መሥፈርቶች መሠረት ከተጠቆሙት ሰዎች ውስጥ አስራ አራት ኮሚሽነር ሊሆኑ የሚችሉ ዕጩዎችን በመለየት የዕጩዎቹን ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ በማድረግ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤

3/ የሚያዘጋጀው የዕጩዎች ዝርዝር የፆታ እና ሌሎች የብዝሃነት መገለጫዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፤

4/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ አመራሮች እና ተወካዮች ጋር በቀረቡት ዕጩዎች ላይ ምክክር ያደርጋል፤

5/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፭4) ሥር የተገለፀውን ምክክር ካደረገ በኋላ ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል እንደ አስፈጊነቱ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ኮሚሽነር ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ዕጩዎችን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያቀርባል።

## 13. ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች

ማንኛውም ኮሚሽነር ሆኖ የሚሾም ሰው የሚከተሉትን መሥፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

1/ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

2/ ሁሉንም ሃይማኖቶች፣ የተለያዩ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችን እና ሕዝቦችን በእኩል ዓይን የሚያይ፤

3/ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፤

4/ ለአገራዊ መግባባት ጉልህ አስተዋፅዖ ሊያበረክት የሚችል ፤

5/ መልካም ሥነ-ምግባርና ስብዕና ያለው፤

6/ በሕዝብ ዘንድ ዓመኔታ ያለው፣

7/ በከባድ ወንጀል ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ያልተላለፈበት ፤

8/ የኮሚሽኑን ሥራ በአግባቡ ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ብቃት ያለው፤

9/ ሙሉ ጊዜውን ለኮሚሽኑ ስራ ለማዋል ፍቃደኛ የሆነ።

## 14. የኮሚሽነሮች ደመወዝና ጥቅማጥቅም

የኮሚሽነሮች ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ለመንግሥት ከፍተኛ ተሿሚዎች በተፈቀደው ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም አግባብ ይፈፀማል።

15. **የኮሚሽነሮች መብትና ግዴታ**

1/ ማንኛውም ኮሚሽነር የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል: -

(ሀ) ያለመከሰስ መብቱ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካልተነሳ ወይም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር በኮሚሽነርነት በሚያገለግልበት ወቅት በወንጀል ያለመከሰስ መብት አለው፤

(ለ) በኮሚሽኑ ምክር ቤት ስራ ላይ በነፃነት የመሳተፍና ድምፅ የመስጠት፤

(ሐ) ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን የማግኘት እና የመመልከት፤ እና

(መ) የኮሚሽኑ ምክር ቤት በሚወስነው አግባብ የኮሚቴ ሥራዎች እና ሌሎች ሥራዎች ላይ የመሳተፍ።

2/ ማንኛውም ኮሚሽነር የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል: -

(ሀ) የኮሚሽኑን ተግባር እና ኃላፊነት በተገቢ ሁኔታ መፈፀም፤

(ለ) ሙሉ ጊዜውን ለኮሚሽኑ ሥራ የማዋል፤

(ሐ) የጥቅም ግጭትን የማስወገድ፤

(መ) በሥራ ሂደት ያገኘውን ምስጢር የመጠበቅ፤

(ሠ) የኮሚሽኑን ገለልተኛነት፣ መልካም ስም እና ክብር ከሚያጎድፉ እና ውጤታማነትን ከሚያደናቅፍ ድርጊት የመቆጠብ፤

(ረ) ሌሎች የኮሚሽኑን ሥርዓቶች እና ደንቦች የማክበር።

16. **ኮሚሽነሮች ከኃላፊነት ስለሚነሱበት ሁኔታ**

1/ ማንኛውም ኮሚሽነር በሚከተሉት ሁኔታዎች ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል፡-

(ሀ) በህመም ምክንያት መደበኛ ተግባሩን ማከናወን ባለመቻል፤

(ለ) ግልፅ የሆነ የብቃት ማነስ ከታየበት፤

(ሐ) ከባድ የሥነምግባር ጉድለት ከታየበት፤

(መ) ያለበቂ ምክንያት ለተከታታይ አስር ቀኖች በሥራ ገበታው ላይ ካልተገኘ፤ ወይም

https://chilot.me

(ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 13 ስር ከተመለከቱት መሥፈርቶች ውስጥ በሹመት ወቅት ኮሚሽነሩ ያላሟላው መሥፈርት መኖሩ ከተረጋገጠ።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ኮሚሽነር ከኃላፊነት የሚነሳው ማንኛውም ማስረጃ ባለው ወገን ጠያቂነት የቀረበ ማመልከቻ አሳማኝ ነው ብሎ አፈጉባዔው ተቀብሎ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ የሚያስተላልፈው ጥያቄ ወይም ከአንድ ሶስተኛ በማያንሱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አነሳሽነት ወይም ከሦስት በማያንሱ ኮሚሽነሮች ጥያቄ መሠረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያስተላለፈው ውሳኔ ይሆናል።

**17. ኃላፊነትን በገዛ ፍቃድ ስለመልቀቅ**

ማንኛውም ኃላፊነቱን በገዛ ፍቃዱ መልቀቅ የሚፈልግ ኮሚሽነር የሁለት ወር የፅሑፍ ቅድመ ማስጠንቀቅያ ለኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባዔ በመስጠት ሊለቅ ይችላል፤

**18. ኮሚሽነር ስለመተካት**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 16 እና 17 መሠረት ኮሚሽነር ከኃላፊነት ሲነሳ ወይም ሲለቅ ወይም በሞት ምክንያት ሲለይ ኮሚሽነር በሚሾምበት ሥርዓት እና መሥፈርቶች መሠረት ተተኪ ኮሚሽነር ይሾማል።

## ክፍል አራት

## ስለኮሚሽኑ ምክር ቤት ፤ ዋና ኮሚሽነር እና ፅሕፈት ቤት

**19. የኮሚሽኑ ምክር ቤት**

የኮሚሽኑ ምክር ቤት ሁሉንም ኮሚሽነሮች በአባልነት ያቀፈ ነው።

**20. የኮሚሽኑ ምክር ቤት ተግባር እና ሥልጣን**

የኮሚሽኑ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የሕዝብ ምክክር የሚደረግባቸውን አጀንዳዎች በዝርዝር በመፈተሸ ምክክር እንዲደረግባቸው መወሰን፤

2/ በኮሚቴዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ እና በሕዝባዊ ውይይቶች የተገኙ ምክረ ሃሳቦችን በዝርዝር በመፈተሸ እና በማጠናቀር ለመንግሥት እንዲቀርብ ማፅደቅ፤

3/ የፅሕፈት ቤቱን አመታዊ በጀትና ዕቅድ መርምሮ የማፅደቅ፤

4/ የፅሕፈት ቤቱን አጠቃላይ ሪፖርት መርምሮ የማፅደቅ፤

https://chilot.me

5/ አስፈላጊ ኮሚቴዎችን የማቋቋም፤

6/ በክልሎች የፅሕፈት ቤቱን ቅርንጫፍ ፅሕፈት ቤቶች እንዲቋቋሙ የመወሰን፤

7/ የፅሕፈት ቤቱን የኦዲት ግኝት መርምሮ የማፅደቅ፤

8/ የምክርቤቱ ዋና ኮሚሽነርና ምክትል ዋና ኮሚሽነር በተመሳሳይ ጊዜ በሥራ ገበታቸው ላይ ለተከታታይ አስር ቀኖች ካልተገኙ ከአባላቶቹ መካከል ጊዜያዊ ሰብሳቢ የመምረጥ፤

9/ የፅሕፈት ቤቱን መዋቅራዊ አደረጃጀት የማፅደቅ፤

10/የፅሕፈት ቤቱን ሃላፊ ሹመት የማፅደቅ፤

11/አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት፤

12/የኮሚሽነሮች የሥነ ምግባር መመሪያ የማውጣት፤

13/የፅሕፈት ቤቱን መተዳደርያ ደንብ የማውጣት።

## 21. የዋና ኮሚሽነር ተግባር እና ሥልጣን

የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል፦

1/ የኮሚሽኑን ምክርቤት በሰብሳቢነት ይመራል፤

2/ አጠቃላይ የኮሚሽኑን ስራ የመምራት፤

3/ የኮሚሽኑን ምክርቤት ስብሰባ አጀንዳዎችን የማቅረብ፤

4/ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት፤

5/ የፅሕፈት ቤቱን አጠቃላይ ስራ የመቆጣጠር፤

6/ ኮሚሽኑን በመወከል ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት የማድረግ፤

7/ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ሪፖርቶችን የማቅረብ፤

8/ የኮሚሽኑን የፅሕፈት ቤት ኃላፊ ዕጩ ለምክር ቤት አቅርቦ የማሾም፤

9/ የኮሚሽኑን ሠራተኞች የመቅጠር እና የማስተዳደር፤

10/የኮሚሽኑን በጀት ጥያቄ ከገንዝብ ሚኒስቴር ጋራ በማዘጋጀት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፤

11/ሌሎች በኮሚሽኑ ምክር ቤት የሚሰጡትን ተግባራት የማከናወን።

## 22. የምክትል ዋና ኮሚሽነር ተግባር እና ሥልጣን

የኮሚሽኑ ምክትል ዋና ኮሚሽነር የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል: -

1/ ዋናው ኮሚሽነር በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

https://chilot.me

2/ በዋናው ኮሚሽነር የሚሰጡትን ተግባራት ይፈጽማል።

**23. ስለኮሚሽኑ ፅሕፈት ቤት**

1/ የኮሚሽኑ ፅሕፈት ቤት ኮሚሽነር ባልሆነ ኃላፊ ይመራል፤

2/ ፅሕፈት ቤቱ ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፤

3/ ፅህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለዋናው ኮሚሽነር ይሆናል።

**24. የኮሚሽኑ ፅሕፈት ቤት ተግባር እና ኃላፊነት**

የኮሚሽኑ ፅሕፈት ቤት የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል: -

1/ የኮሚሽኑን ፅህፈት ቤት መዋቅራዊ አደረጃጀት ለይቶ ለኮሚሽኑ ምክር ቤት አቅርቦ የማፀደቅ፤

2/ ለኮሚሽኑ አጠቃላይ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት የመስጠት፤

3/ ለኮሚሽኑ ተግባር እና ኃላፊነት አስፈላጊ የሆኑትን ግብዓቶችን እና ሌሎች አገልግሎቶችን የማቅረብ፤

4/ የኮሚሽኑን ቃለ ጉባዔዎች፤ ውሳኔዎች፤ የሂሳብ መዛግብት እና ሌሎች መረጃዎችን በሚገባ አደራጅቶ የመያዝ፤

5/ የኮሚሽኑን በጀት በማዘጋጀት ዋና ኮሚሽነሩን ማገዝ፤ እና

6/ ሌሎች በምክር ቤቱ ወይም በዋና ኮሚሽነሩ የሚሰጡትን ተግባራት ማከናወን።

**25. የፅሕፈት ቤቱ ኃላፊ ተግባር እና ኃላፊነት**

1/ የፅሕፈት ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል፤ -

(ሀ) የፅሕፈት ቤቱን መዋቅራዊ አደረጃጀት ለይቶ ለኮሚሽኑ ምክር ቤት አቅርቦ የማፀደቅ፤

(ለ) የፅሕፈት ቤቱን ተግባራት አስመልክቶ ለዋናው ኮሚሽነር አና ለኮሚሽነሮች ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ፤

(ሐ) የፅሕፈት ቤቱን የሥራ ዕቅድ ለኮሚሽኑ ር ምክር ቤት አቅርቦ የማፀደቅ፤ እና

(መ) በዚህ አዋጅ ለፅሕፈት ቤቱ የተሰጡትን ተግባራት እና ሥልጣን በመምራት የማስተዳደር።

2/ የፅሕፈት ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነት ለኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

https://chilot.me

**26. <u>የበጀት ምንጭ</u>**

1/ የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች ሕጋዊ ምንጮች ማግኘት ይችላል።

3/ የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በኮሚሽኑ ምክር ቤት በሚፀድቅ የውስጥ ደንብ መሠረት ኮሚሽኑ በጀቱን የማስተዳደር ሙሉ ነፃነት አለው።

**27. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1/ ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

2/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**28. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1/ የሚንስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፤

2/ የኮሚሽነሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**29. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚያቀርበው ማንኛውም ህጋዊ ጥያቄ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት።

**30. ተፈፃሚነተ ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም

**31. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከ……… ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ …. ቀን 2014 ዓ.ም.

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

https://chilot.me